**ፍሰሐ- ወ -ህይወት**

**ፍሰሐ ወ ህይወት**
**ለምለም በረሀ-ገነት**
**ሁሉ የሚማልልላት**
**ሊወስዳት ሊወዳት**
**የራሱ ሊያደርጋት**
**ዘላለም ሊያኖራት:**

**ከተደበቀችበት ጥሻ**
**ከመሸገችበት ዋሻ**
**ከተሰገበችበት ሰገባ**
**ክንብንብ ጥርዝ ካባ:**
**ካቆለቆለችበት አዘቅት**
**ከጭጋግዋ ጥልመት:**
**አንገትዋን አንቄ**
**አካሏን ጨምቄ**
**በሽብልቅ ሸብልቄ**
**በጠገራ ሰንጥቄ**
**በወረንጦ መንጥቄ**
**በካራ መትሬ**
**በካስማ ወድሬ**
**በጠፍር ሰትሬ**
**በአውታር ገትሬ**
**ከስሯ ሰቅስቄ**
**ላስቀራት አምቄ**
**ላደርጋት የራሴ**
**የሥጋ የነፍሴ:**
**ተጋሁ ተንገታገትኩ**
**ወጣሁና ወረድኩ**
**ሌትና ቀን ማሰንኩ**
**ቆምኩ ተምበረከኩ**
**ተቀኘ ወደ ግራ**
**እንደ ፍየል ጭራ**
**ቁልቁለት ተራራ**
**እሩጫ በረራ**
**አንዳችም ላልሰራ**
**ላልወጣ ከተራ ....**

**ጥር 12 2000**
**በላቸው ገላሁን**

**Back to Meskot**

---

***The views reflected in the above poem/article are solely of the author and are not necessarily shared by** Meskot. **You may contact Belachew Gelahun for comments at** belachewg@yahoo.com.*